Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL



## የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

# የወላጅ—መምህር ኮንፈረንስ

**ይዘጋጁ!** የልጅዎ ትምህርት ቤት በኖቬምበር ለወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንስ ይጋብዝዎታል። የእርስዎ ልጅ በትምህርት ቤት በአካደሚክ እና በማህበራዊ ግንኙነት ስለሚያሳየው/ስለምታሳየው ሁኔታ ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ለመወያየት ጥሩ እድል የሚያገኙበት ጊዜ ነው። ልጅዎ ወደሚማርበት/ወደምትማርበት ትምህርት ቤት መምጣት ሁል ጊዜ መልካም መሆኑን ያስታውሱ!

**እኛ የምናውቀው:** መምህራኖቻቸው፣ ወላጆቻቸው እና ተንከባካቢዎቻቸው ሲያግዟቸውና አብረው ሲሰሩ ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ ይሰራሉ። እነዚህን ስብሰባዎች እንደማስፈራሪያ ሊሰማቸው እንደሚችልም እናውቃለን። ይህ የውይይት ጥያቄ ዝርዝር ልጅዎ እንዲሳካለ(ላ)ት ለመርዳት የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት ይረዳዎታል። የራስዎን ጥያቄዎችም መጨመር ይችላሉ።

**ከልጄ አስተማሪ ጋር ለመገናኘት የሚኖረኝ ዕድል ይሄ ብቻ ነው?** በትምህርት አመቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ከልጅዎ አስተማሪ ጋር መነጋገር ይችላሉ። የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንስ እስከሚደረግ መጠበቅ የለብዎትም። የወላጅ-መምህር ኮንፈረንሶች በሚደረጉበት ጊዜ አስተርጓሚ ማግኘት ይቻላል። አስተርጓሚ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎን ለልጅዎ አስተማሪ አስቀድመው ይንገሩ።

### የልጄን መምህር ምን አይነት ጥያቄዎች መጠየቅ አለብኝ?


- ☐ ልጄ በክፍል ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ እየሰራ(ች) ነው?
- ☐ ልጄ ኮሌጅ ለመማር እና ስኬታማ ለመሆን በሚያስችል ደረጃ ትክክለኛ መንገድ ላይ ነው/ናት?
- ☐ ልጄ የሙያ ፕሮግራም ሠርተፊኬት ለመከታተል ትክክለኛ ትምህርት እየወሰደ(ች) ነው?
- ☐ ልጄ ክፍል ውስጥ በውይይቶች እና በእንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፋል/ትሳተፋለች?
- ☐ ልጄ ጥሩ እየሰራ(ች) ያለው ምን እንደሆነ እና ምን እንደሚያስቸግረው(ራት) የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ሊነግሩኝ ይችላሉ?
- ☐ ልጄን ለመርዳት ትምህርት ቤቱ ምን ተጨማሪ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል?
- ☐ ከትምህርት ቤት ሠዓት በኋላ ልጄን የሚጠቅሙ ፕሮግራሞች፣ ክለቦች ወይም እንቅስቃሴዎች አሉ?
- ☐ ልጄን በትምህርት ቤት ሥራው(ዋ) ለመርዳት በቤት ውስጥ ምን ማድረግ እችላለሁ?

### እንዲሁም የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ:-

- ስለልጅዎ ፍላጎቶች ለአስተማሪው(ዋ) ይግለጹ።
- ልጅዎ ማንኛውም ስሜታዊ ወይም የጤና ችግሮች ካለበ(ባ)ት ለአስተማሪው ያስረዱ።

ይቀጥላል

# ከስብሰባው በኋላ፡-



AskMCPS

**በተደጋጋሚ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልሶችን ያግኙ**
በቀን 24 ሰዓት፤ በሳምንት 7 ቀናት፤ በማንኛውም ቋንቋ መልሶችን ማግኘት ይችላሉ።

- AskMCPS በስልክ ቁጥር 240-740-3000 (በማንኛውም ቋንቋ) ይደውሉ።
- En español: 240-740-2845
- በዚህ አድራሻ ኢሜል ያድርጉ፡- AskMCPS@mcpsmd.org (any language)

https://www.montgomeryschoolsmd.org/askmcps-faqs/

**የልጄን ስራ በደንብ ለመከታተል ተመራጭ መንገድ ምንድነው?**
"ParentVue" ይመዝገቡ። ይህ ለአጠቃቀም ቀላል የሆነ ለሞባይል ተስማሚ መተግበሪያ ነው። ለመጀመር ወይም አካውንትዎን እንደገና ለማስጀመር እዚህ ጠቅ ያድርጉ ወይም ከላይ ያለውን QR ኮድ ይጠቀሙ። ለበለጠ መረጃ ወይም የቴክኒክ ድጋፍ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ፡- MCPS ድረገጽ > Parents > Parent Resources > ከዚያ ቀጥሎ Community Tech Support Center Information የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።

**ልጄ የባህሪ፣ የጤና ወይም የስሜታዊነት ችግር ካለበ(ባ)ት ምን ማድረግ አለብኝ?**
ይህን መረጃ ትምህርት ቤቱ እንዲያውቅ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው። የልጅዎ ትምህርት ቤት ካውንስለር ከእርስዎ ጋር መሥራት ይችላል/ትችላለች። እባክዎን ለልጅዎ ካውንስለር ይደውሉ፣ይጻፉ ወይም ኢሜል ያድርጉ።

**ልጄ የቤት ስራ ለመሥራት ስለሚቸገር/ስለምትቸገር እንዴት መርዳት እንዳለብኝ አላውቅም።**
ልጅዎ ከአስተማሪው(ዋ) ጋር እንዲነጋገር/እንድትነጋገር እና እርዳታ እንዲጠይቅ/እንድትጠይቅ ይንገሩ።

ይሄ ካልረዳዎት መደወል፣ኢሜል ማድረግ፣ ወይም ለአስተማሪ ማስታወሻ መጻፍ አለብዎት።

ብዙ ትምህርት ቤቶች ከትምህርት ሠዓት በኋላ ሂሳብ እና እንግሊዝኛ ለማስጠናት ነፃ እገዛ ያደርጋሉ። ትምህርት ቤትዎ ይህን አይነት ድጋፍ የሚሰጥ ከሆነ የልጅዎን መምህር ይጠይቁ። ወላጆች ተጨማሪ እርዳታ ሲያስፈልግ ለመምህሩ(ሯ) መደወል ወይም ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL